# የውጭ አገር መገናኛ ብዙሃን የዜና ወኪሎች እና የውጭ አገር ዜጎች የፊልም ቀረጻ ምዝገባና ፈቃድ አሰጣጥ መመሪያ ቁጥር 900/2014

Foreign Media, News Agencies and Foreign Citizens Film Recording Registration and Licensing Directive No. 900/2014

የኢትዮጵያ መገናኛ ብዙኃን ባለስልጣን
Ethiopian Media Authority

ግንቦት 1፥ 2014

## *መመሪያ ቁጥር 900/2014*

## ***<u>የውጭ ሀገር መገናኛ ብዙሃን ወኪሎች እና የውጭ ሀገር ዜጎች የፊልም ቀረጻ ምዝገባና ፈቃድ አሰጣጥ መመሪያ</u>***

የዓለም አቀፉ ሚዲያና ማህበረሰብ የኢትዮጵያን ታሪካዊ ቅርሶችና ባህላዊ እሴቶች፣ እንዲሁም ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ሁኔታዎች በትክክል ተገንዝቦ ለውጭው ዓለም በማስተዋወቅ ረገድ የውጭ ሀገር የመገናኛ ብዙሃን ወኪሎችና የፊልም ቀራጮች ጉልህ ሚና የሚጫወቱ በመሆኑ፤ እንዲሁም የአገሪቱን ጥቅምና ሉአላዊነት ያከበረ የዜና ዘገባና የፊልም ቀረጻ ስራ መስፋፋቱ ለአገሪቱ በጎ ገጽታ ያለውን ጠቀሜታ በመገንዘብ፤

በመገናኛ ብዙሃን አዋጅ ቁጥር 1238/2013 አንቀጽ 6(14) መሰረት የውጭ ሀገር መገናኛ ብዙሃን እና የዜና ወኪሎች በአገራችን ለመንቀሳቀስ በቅድሚያ መመዝገብ ያለባቸው በመሆኑ፤ እንዲሁም በኢትዮጵያ ውስጥ ተራኪ ወይም ዘጋቢ ፊልም ለማንሳት በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 66/1992 አንቀጽ 5 መሰረት ፈቃድ ማግኘት የሚያስፈልግ በመሆኑ፤ ግልጽ፣ ቀልጣፋ እና ተጠያቂነት የሰፈነበት የምዝገባና ፈቃድ አሰጣጥ ስርዓት ለመዘርጋት፤

የቀድሞ የመንግስት ኮሙኒኬሽን ጉዳዮች ጽ/ቤት መታጠፍን ተከትሎ ከጠቅላይ ሚኒስቴር ጽህፈት ቤት በቁጥር መ10-11/830/1 ጥቅምት 15 ቀን 2011ዓ.ም. በተላለፈው ሰርኩላር የዘጋቢ ወይም ተራኪ ፊልም የፈቃድ አሰጣጥ ስራ ወደ የኢትዮጵያ መገናኛ ብዙሃን ባለስልጣን ተላልፎ እንዲሰራ በመወሰኑ በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 66/1992 አንቀጽ 13 እና በመገናኛ ብዙሃን አዋጅ ቁጥር 1238/2013 አንቀጽ 90(2) መሰረት ይህ መመሪያ በባለስልጣኑ ቦርድ ወጥቷል፡፡

### ***<u>ክፍል አንድ</u>***

### ***<u>ጠቅላላ</u>***

1. ***<u>አጭር ርዕስ</u>***

***ይህ መመሪያ "የውጭ ሀገር መገናኛ ብዙኃን ወኪሎች እና የውጭ አገር ዜጎች የፊልም ቀረጻ ምዝገባና ፈቃድ አሰጣጥ መመሪያ ቁጥር 900/2014"*** ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. ***<u>ትርጓሜ</u>***

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ፡-

1/ ***"ባለሥልጣን"*** ማለት የኢትዮጵያ መገናኛ ብዙኃን ባለሥልጣን ነው፡፡

2/ ***"የውጭ ሀገር መገናኛ ብዙኃን ወኪል"*** ማለት ለውጭ ሀገር የሚዲያ ተቋም ዘገባ ለማሰባሰብና ዘጋቢ ፊልም ለመስራት ወደ ኢትዮጵያ የሚመጣ ወይም

በኢትዮጵያ ነዋሪ የሆነ የዜና አገልግሎት፣ የሕትመት፣ የፎቶ-ግራፍ፣ የመገናኛ ብዙሃን እና የድረ-ገጽ ባለሙያ ማለት ነው፡፡

3/ ***"ጊዜያዊ የዜና ወኪል ምዝገባ"*** ማለት የውጭ ሀገር የመገናኛ ብዙኃን ወኪል ወደ ኢትዮጵያ በመምጣት ከሦስት ወር ላልበለጠ የቆይታ ጊዜ ውስጥ ዘገባዎችን አሰባስቦ ወደ መጣበት አገር ለመመለስ እንዲችል በዚህ መመሪያ መሰረት የሚደረግ ምዝገባ ነው፡፡

4/ ***"ቋሚ የዜና ወኪል ምዝገባ"*** ማለት የውጭ ሀገር የሚዲያ ወኪል ወደ ኢትዮጵያ በመምጣት ከሶስት ወር እስከ አንድ አመት የቆይታ ጊዜ ውስጥ ዘገባዎቹን አሰባስቦ ወደመጣበት አገር ለመመለስ እንዲችል በዚህ መመሪያ መሰረት የሚደረግ ምዝገባ ነው፡፡

5/ ***"ጊዜያዊ የፊልም ቀረጻ ፈቃድ"*** ማለት የውጭ ሀገር ዜጎች ወይም የፊልም ባለሙያዎች ወደ ኢትዮጵያ በመምጣት ከሦስት ወር ባልበለጠ የቆይታ ጊዜ ውስጥ ፊልሞችን ቀርጸው ወደ መጡበት አገር ለመመለስ እንዲችሉ በዚህ መመሪያ መሰረት የሚሰጥ ፈቃድ ነው፡፡

6/ ***"ዘጋቢ ወይም ዶክመንተሪ ፊልም"*** ማለት አንድ የውጭ አገር ዜጋ ወይም የፊልም ባለሙያ ወደ ኢትዮጵያ በመምጣት ተፈጥሮን፣ ታሪክን፣ ባህልን፣ ክብረበዓልን፣ ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ እንቅስቃሴዎችንና የመሳሰሉትን በፊልም የመቅረጽ አላማን ይዞ የሚቀረጽ ፊልም ነው፡፡

7/ ***"ተራኪ ወይም ልብ ወለድ ፊልም"*** ማለት በልቦለድ ድርሰት ላይ ተመስርቶ ተዋንያንን በማሳተፍ የሚቀረጽ ማንኛውም ፊልም ነው።

8/ **"አመልካች"** ማለት ተራኪ ወይም ዘጋቢ ፊልም ለመቅረጽ ፈቃድ እንዲሰጠው ወይም የዜና ወኪልነት ስራ ላይ ለመሰማራት የምዝገባና የዕውቅና ምስክር ወረቀት ወይም መታወቂያ ባጅ ወይም ፈቃድ እንዲሰጠው በባለሥልጣኑ የተዘጋጀውን የማመልከቻ ቅፅ ሞልቶ ያመለከተ ሰው ነው፡፡

9/ ***"የፈቃድና ምዝገባ የሥራ ክፍል"*** ማለት በዘገባ ስራ ለመሰማራት ወይም ተራኪ ወይም ዘጋቢ ፊልም ለመስራት ምዝገባ ወይም ፈቃድ ለማግኘት የሚቀርብ ማመልከቻን ተቀብሎ መሟላት ያለባቸው መስፈርቶች መሟላታቸውን በማጣራት የሚመዘግብ ወይም ፈቃድ የሚሰጥ በባለሥልጣኑ ውስጥ የተቋቋመ የሥራ ክፍል ነው፡፡

10/ ***"ቦርድ"*** ማለት የኢትዮጵያ የመገናኛ ብዙሃን ባለሥልጣን ቦርድ ነው፡፡

11/ ***"የባለሥልጣኑ የበላይ ኃላፊ"*** ማለት የባለሥልጣኑ ዋና ዳይሬክተር ወይም ዋና ዳይሬክተሩ በማይኖርበት ጊዜ ምክትል ዋና ዳይሬክተር ነው፡፡

12/ ***"አዋጅ"*** ማለት የመገናኛ ብዙሃን አዋጅ ቁጥር 1238/2013 ነው፡፡

13/ ***"ደንብ"*** ማለት የውጭ ሀገር ዜጎች ኢትዮጵያ ውስጥ ፊልም ስለሚቀርጹበት ሁኔታ የወጣ ደንብ ቁጥር 66/1992 ነው፡፡

14/ ***"ሰው"*** ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፡፡

15/ ሌሎች በአዋጁ የተሰጡ ትርጉሞች ለዚህ መመሪያም ያገለግላሉ፡፡

16/ በወንድ ጾታ የተገለጸው አገላለጽ ሴትንም ያካትታል፡፡

### 3. *የተፈጻሚነት ወሰን*

ይህ መመሪያ ለውጭ መገናኛ ብዙሃን ዘገባ ለማሰባሰብ በጊዜያዊ ወይም በቋሚ የዜና ወኪልነት ወደ ኢትዮጵያ በሚመጡ ወይም ተቀማጭነታቸው ኢትዮጵያ ውስጥ በሆነ የዜና ወኪሎች እንዲሁም ዘጋቢ ወይም ተራኪ ፊልም ለመስራት ከውጭ አገር በሚመጡ የውጭ ዜጎች ላይ ተፈጻሚ ይሆናል።

## *ክፍል ሁለት*
## *የውጭ አገር መገናኛ ብዙኃን የዜና ወኪል የምዝገባ ምስክር ወረቀት ወይም ፈቃድ አሠጣጥ ሥነ-ሥርዓት*

### 4. *አጠቃላይ*

1/ ማንኛውም ሰው ከባለስልጣኑ የውጭ ሚዲያ የዜና ወኪልነት የምዝገባ ምስክር ወረቀት ወይም ፈቃድ ሳያገኝ የውጭ መገናኛ ብዙኃን የዜና ወኪል በመሆን ኢትዮጵያ ውስጥ መዘገብ አይችልም፡፡

2/ ማንኛውም በኢትዮጵያ ውስጥ ለመዘገብ የሚፈልግ የውጭ መገናኛ ብዙኃን የዜና ወኪል በአዋጁና በዚህ መመሪያ መሰረት የተዘረዘሩትን መረጃዎች በማሟላት የምዝገባ የምስክር ወረቀት እንዲሰጠው ለባለስልጣኑ ማመልከት አለበት፡፡

3/ ማንኛዉም በውጭ አገር ተቋቁሞ ወይም ፈቃድ አግኝቶ የሚንቀሳቀስ መገናኛ ብዙሃን በኢትዮጵያ ውስጥ ቅርንጫፍ ወይም ስቱዲዮ ከፍቶ ለመንቀሳቀስ ከፈለገ ከባለሥልጣኑ የብሮድካስት ፈቃድ ማውጣት አለበት፡፡

### 5. *ስለማመልከቻ ቅፅ*

ባለሥልጣኑ የሚከተሉትን ጉዳዮች የያዘ የማመልከቻ ቅፅ ያዘጋጃል፡፡ የማመልከቻ ቅፁንም በድረ-ገፁ ተደራሽ በማድረግ ተሞልቶ እንዲቀርብ አማራጭ መንገድ ይፈጥራል፡፡

1/ የመጣበት ወይም የወከለውን የውጭ አገር መገናኛ ብዙኃን ስም፣

2/ መገናኛ ብዙሃኑ የተቋቋመበት አገር፣

3/ ዘገባውን ለመስራት ተቋሙ የሚያሰማራውን የዜና ወኪል ስም፣ የስራ መደብ፣ ዜግነት፣ የፓስፖርት ቁጥር፣ ስልክ ቁጥር እና የኢሜል አድራሻ፤

### 6. *የማመልከቻ አቀራረብ*

1/ የውጭ አገር መገናኛ ብዙኃን የዜና ወኪል ወደ ሀገር ውስጥ ከመግባቱ በፊት አግባብነት ያለው ኃላፊ የፈረመበትንና የድርጅቱ ማሕተም ያረፈበት ማመልከቻን በአንቀጽ 7 ከተጠቀሱት ዝርዝር ሰነዶች ጋር በማያያዝ ቢያንስ ከ15 ቀን በፊት በአቅራቢያው ለሚገኝ የኢፌዲሪ ኤምባሲ ወይም ቆንስላ

ጄኔራል ጽሕፈት ቤት የፐብሊክ ዲፕሎማሲ የሥራ ክፍል በአካል በመቅረብ ወይም በኢ-ሜል ወይም በፋክስ ወይም በሌላ አመቺ ዘዴ ማቅረብ ወይም መላክ አለበት፡፡

2/ ኢትዮጵያ ውስጥ የሚገኝ ማንኛውም ድርጅት የዜና ወኪል በማስመጣት ዘገባ ማሰራት ሲፈልግ ከዚህ በታች በአንቀጽ 7 የተጠቀሱትን ማስረጃዎች አያይዞ ቢያንስ ከ15 ቀን በፊት የውጭ ሀገር የመገናኛ ብዙኃን የዜና ወኪሉ ለሚኖርበት የኢፌዲሪ ኤምባሲ ወይም ቆንስላ ጄኔራል ጽሕፈት ቤት የፐብሊክ ዲፕሎማሲ የሥራ ክፍል በኢ-ሜል፣ በፋክስ ወይም በሌላ አመቺ ዘዴ መላክ ይኖርበታል፡፡

3/ የኢፌዲሪ ኤምባሲ ወይም ቆንስላ ጄኔራል ጽሕፈት ቤት የፐብሊክ ዲፕሎማሲ ሥራ ክፍል ማመልከቻው የተሟላ መሆኑን አረጋግጦ፣ የማስረጃዎቹን አግባብነት አጣርቶ፣ ስለዘገባው ጠቀሜታና መገናኛ ብዙኃን ዜና ወኪሉ ከዚህ ቀደም ስላወጣቸው የሚዲያ ውጤቶች አወንታዊነትና አሉታዊነት አስመልክቶ ያለውን አስተያየትና ተያያዥ መረጃዎችን በማካተት በሸፈ ደብዳቤ በ5 ቀናት ውስጥ በኢፌዲሪ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር በኩል ለባለሥልጣን መስሪያ ቤቱ ይልካል፡፡

4/ የኢፌዲሪ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ማመልከቻውን ከነአባሪ ሰነዱ እንደደረሰው የተሟላ መሆኑን በማረጋገጥ ቢበዛ በሁለት የስራ ቀናት ውስጥ ለባለስልጣኑ ይልካል፡፡

5/ ለአስቸኳይ ስብሰባ፣ ለሀገራት የሁለትዮሽ ውይይት፣ ለከፍተኛ ባለስልጣናት ይፋዊ ጉብኝት፣ ተቀማጭነታቸው ኢትዮጵያ ውስጥ ከሆኑ ዓለም አቀፍ ድርጅቶች ባለስልጣናት ጋር ለሚመጡ የውጭ ሀገር የመገናኛ ብዙኃን የዜና ወኪሎች የጋዜጠኝነት ቪዛ ጥያቄ፣ ተቀማጭነታቸው አዲስ አበባ የሆነ የተለያዩ ሀገራት ኤምባሲዎችና ኢትዮጵያ ውስጥ ከሚገኙ የተለያዩ አለም አቀፍና አህጉራዊ ድርጅቶች አማካይነት የሚቀርብ የዜና ወኪል ፈቃድ ጥያቄ በኢፌዲሪ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር በኩል ለባለስልጣኑ ይቀርባል፡፡

6/ በባለስልጣኑ ይሁንታን አግኝተው የጋዜጠኝነት ቪዛ እንዲሰጣቸው ከኢሚግሬሽን ዜግነት እና ወሳኝ ኩነት ምዝገባ ኤጀንሲ ደብዳቤ ሲጻፍ ለክትትል እንዲረዳ የመገናኛ ብዙኃን ፈቃድና ምዝገባ ክፍል ለኢፌዲሪ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር በግልባጭ ያሳውቃል፡፡

7/ የቋሚ የዜና ወኪልነት ጥያቄን በተመለከተ የውጭ ሃገር የሚዲያ ተቋሙ ለሚኖርበት የኢትዮጵያ ኤምባሲ ማመልከቻ ቀርቦ በኢፌዴሪ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ቃል-አቀባይ ጽሕፈት ቤት በኩል ለባለስልጣኑ የበላይ ኃላፊ ቀርቦ ተቀባይነት ሲያገኝ የሚፈቀድ ይሆናል።

7. *ከማመልከቻው ጋር መያያዝ የሚገባቸው ዝርዝር ሰነዶች*

1/ዘገባውን ለመስራት የውጭ መገናኛ ብዙኃን የሚያሰማራውን የዜና ወኪል ስም፣ ዜግነት፣ የፓስፖርት ቁጥር እና ሲቪ የያዘ ዝርዝር እና የፓስፖርትና የሙያ መታወቂያ ኮፒ፤

2/ ኢትዮጵያ ውስጥ የሚቆይባቸውን ቀናትና የሚዘዋወርባቸውን ሥፍራዎች የሚገልጽ ሰነድ፣

3/ ወደ ኢትዮጵያ የሚገባበት እና ከኢትዮጵያ የሚወጣበትን ቀን፣ ሰዓት እና በአየር ትራንስፖርት የሚመጣ ከሆነ የአውሮፕላን በረራ ቁጥር የያዘ ማስረጃ፣

4/ የሚዘግበውን ጉዳይ የሚያተኩርባቸው ጉዳዮች እና ዓላማ በዝርዝር የሚያስረዳ ጽሁፍ፣

5/ አመልካቹ ለዘገባው ሥራ የሚጠቀምባቸው የሚዲያ መገልገያ መሣሪያዎች ዝርዝር 2 ቅጂ እና ስራውን ሲያጠናቅቅ በዝርዝሩ ላይ የተመለከቱትን የሙያ መገልገያ መሣሪያዎችን ይዞ እንደሚወጣ ግዴታ መግባቱን የሚገልጽ በጽሁፍ የተደገፈ ሰነድ፣

6/ የሙያ መሳሪያዎቹ ዝርዝር፤ የመሳሪያዎቹን ስሪት ወይም ሞዴል፣ ልዩ መለያ ቁጥር /Serial No/፣ ብዛት እና እያንዳንዳቸው የተገዙበትን ዋጋ በማካተት ማቅረብ አለበት፡፡

8/ *አመልካቹ ፈቃድ ወይም ምዝገባ ለማግኘት ለባለስልጣኑ ማቅረብ ያለበት ሰነዶች*

1/ የዜና ወኪሎች ኦሪጅናል ደብዳቤውን፣ አንድ ጉርድ ፎቶ-ግራፍ (3x4 ሳ.ሜ) የራሱንና የቡድኑን ፓስፖርትና የሙያ መታወቂያ ይዞ በባለስልጣን መስሪያ ቤቱ በግንባር በመቅረብ ከዚህ መመሪያ ጋር በአባሪነት የተያያዘውንና የተዘጋጀውን ለጊዜያዊ ዘገባ ወይም ለቋሚ ዜና ወኪልነት የተዘጋጀውን ቅፅ -1- መሙላት አለበት፣

2/ አመልካቹ የማመልከቻ ቅጹን ከመሙላቱና የመመዝገቢያ ክፍያ ከመፈጸሙ በፊት የጸና ፓስፖርት፣ የጋዜጠኝነት ቪዛ ያለው እንዲሁም በሕጋዊ መንገድ ተመዝግቦ ወደ ሀገር ውስጥ የገባ መሆኑ የሚያረጋግጥ ሰነድ ማቅረብ አለበት፣

9/ *ለመንግሥት የበላይ ኃላፊዎች ስለሚቀርብ ቃለ-መጠይቅ*

በክፍል ሁለት አንቀጽ 8 ላይ የተገለጸው እንደተጠበቀ ሆኖ፦

1/ ለክቡር ፕሬዝዳንት፤ ለክቡር ጠቅላይ ሚኒስትሩ ወይም ለሌሎች ከፍተኛ የመንግስት ባለሥልጣናት የቃለ-መጠይቅ የፈቃድ ጥያቄ በመንግስት ኮሙዩኒኬሽን አገልግሎት ወይም በሚመለከተው አካል ተቀባይነት ሲያገኝ የምዝገባ አገልግሎት ለማግኘት ለባለስልጣኑ በሸኚ ደብዳቤ ይላካል፡፡

2 ለክቡር ፕሬዝዳንት፣ ለክቡር ጠቅላይ ሚኒስትሩ ወይም ለሌሎች ከፍተኛ የመንግስት ባለሥልጣናት ቃለ-መጠይቅ ለማድረግ የሚቀርብ የዜና ወኪል ምዝገባ ወይም ፈቃድ ማመልከቻ በጣም አስቸኳይና በልዩ ሁኔታ ሊታይ የሚገባው ካልሆነ በስተቀር ጋዜጠኛው ከመምጣቱ ቢያንስ ከ10 ቀናት በፊት ለባለሥልጣኑ መድረስ ይኖርበታል፡፡

3/ ማመልከቻው የሚይዛቸው መረጃዎች፦

(ሀ) የሚዲያ ተቋሙን የአድማጭ፣ የተመልካች ተደራሽነትና ሽፋን ወይም የህትመት ውጤቱን የኮፒ ሥርጭት መጠን፣

(ለ) የሚዲያ ባለሙያውን የትምህርት ደረጃ፣ የሥራ ልምድና አሁን ያለበትን የሙያ ዓይነትና ደረጃ፣

(ሐ) የሚዲያ ባለሙያው ከዚህ በፊት ኢትዮጵያ ውስጥ መጥቶ የዘገበው ጉዳይ ካለ የዘገባውን ዓይነት፣ ቦታ እና ጊዜ፣

(መ) ቃለ-ምልልሱ የሚያተኩርባቸውን ርዕሰ ጉዳዮች፣

(ሰ) የሚዲያው ዋና መሥሪያ ቤት አድራሻ በሚገኝበት ሀገር ካለው የኢፌዲሪ ኤምባሲ ወይም ቆንስላ ጄኔራል ጽሕፈት ቤት የፐብሊክ ዲፕሎማሲ ሥራ ከሚሰራው አካል እና ከኢፌዲሪ ውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ወይም ከመንግስት ኮሙዩኒኬሽን አገልግሎት የተሰጠ አስተያየት ወይም የድጋፍ ደብዳቤ፣

4/ ለክቡር ፕሬዝዳንት፣ ለክቡር ጠቅላይ ሚኒስትሩ ወይም ለሌሎች ከፍተኛ የመንግስት ባለሥልጣናት የቃለ-መጠይቅ የፈቃድ ወይም ምዝገባ ጥያቄ በባለሥልጣኑ ተቀባይነት ካገኘ ለኮሙዩኒኬሽን አገልግሎት በሸኚ ደብዳቤ ይላካል፡፡

## 10. *<u>የቪዛ ጥያቄን ስለማስተናገድ</u>*

ለዘገባ ስራ ወደ ኢትዮጵያ የሚመጣ የዜና ወኪል በሚከተሉት አሰራር መሰረት የጋዜጠኝነት ቪዛ ወይም አግባብነት ያለዉ ቪዛ ሊኖረው ይገባል፣

1/ ባለሥልጣኑ በዚህ መመሪያ አንቀድ 7፣ 8 እና 9 መሰረት የቀረበለትን ማመልከቻ ከገመገመ በኋላ ጥያቄው የተሟላ ሆኖ ሲያገኘው አመልካቹ የጋዜጠኝነት ቪዛ ወይም አግባብነት ያለዉ ቪዛ እንዲሰጠው ከሶስት የስራ ቀናት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ ከኢሚግሬሽን ዜግነት እና ወሳኝ ኩነት ምዝገባ ኤጀንሲ በደብዳቤ ያሳውቃል፣

2/ ባለሥልጣኑ የኢፌዲሪ ኤምባሲ ወይም ቆንስላ ጄኔራል ጽሕፈት ቤት ከሌለባቸው ሀገራት የሚመጡ የዜና ወኪሎች ቦሌ አለም አቀፍ አውሮፕላን ጣቢያ ሲደርሱ የመዳረሻ የጋዜጠኝነት ቪዛ እንዲሰጣቸው ከኢሚግሬሽን ዜግነት እና ወሳኝ ኩነት ምዝገባ ኤጀንሲ በደብዳቤ ያሳውቃል፣

3/ ኢሚግሬሽን እና ዜግነት ጉዳዮች ዋና መምሪያ የጋዜጠኝነት ቪዛ የተጠየቀላቸው የሚዲያ ባለሙያዎች ከባለስልጣኑ ደብዳቤ ሲደርሰው ቪዛ እንዲያገኙ ጥያቄውን ላቀረበው በውጭ ሀገር የኢፌዲሪ ኤምባሲ ወይም ቆንስላ ጄኔራል ጽሕፈት ቤት ይልካል፤ መላኩንም ለሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ያሳውቃል፣

4/ ባለስልጣኑ የጋዜጠኝነት ቪዛ ጥያቄው ምላሽ ማግኘቱን ይከታተላል፣ የደረሰበትን ለሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ያሳውቃል፣

5/ ባለፈቃዱ ኢትዮጵያ ውስጥ ለመቆየት ቪዛው እንዲራዘምለት ጥያቄ ሲያቀርብና ይህም በባለስልጣኑ ተቀባይነት ሲያገኝ ከኢሚግሬሽን ዜግነት እና ወሳኝ ኩነት ምዝገባ ኤጀንሲ ቪዛው እንዲራዘምለት በደብዳቤ ይጠይቃል፣

6/ ባለስልጣኑ የጋዜጠኝነት ቪዛ ወይም ኢትዮጵያ ውስጥ ለመቆየት የቪዛ ይራዘምልኝ ጥያቄውን ያልተቀበለው እንደሆነ ያልተቀበለበትን ምክንያትና ውሳኔውን በአንድ የሥራ ቀን ውስጥ ለአመልካቹ ማሳወቅ ይኖርበታል፣

7/ ባለስልጣኑን ምንም አይነት ፈቃድ ሳይጠይቅ ከጋዜጠኝነት ቪዛ ውጭ በሆነ ቪዛ ሀገር ውስጥ የገባ እና ለባለስልጣኑ የዘገባ ምዝገባ የሚጠይቅ የውጭ ሀገር የሚዲያ ባለሙያ ፈቃዱ ሳይሰጠው ከኢሚግሬሽን ዜግነት እና ወሳኝ ኩነት ምዝገባ ኤጀንሲ በሚሰጠዉ አቅጣጫ መሰረት አስተዳደራዊ ውሳኔ እንዲሰጠው ይደረጋል፣

8/ ባለስልጣኑ የኬንያና የጂቡቲ ዜግነት ያላቸው የሚዲያ ባለሙያዎች በሀገር ውስጥ የዘገባ ስራ ለመስራት ወደ ሀገራችን መምጣት ሲፈልጉ ኢትዮጵያ ከሁለቱ ሀገራት ጋር ባላት ስምምነት መሰረት ቪዛ አይጠየቁም፡፡

## ክፍል ሶስት
## የተራኪ ወይም ልብ ወለድ እንዲሁም ዘጋቢ ወይም ዶክመንተሪ ፊልም ለመስራት የፈቃድ አሠጣጥ ሥነ-ሥርዓት

11/ *አጠቃላይ*

1/ ማንኛውም የውጭ ዜጋ ከባለስልጣኑ ፈቃድ ሳያገኝ ተራኪ ወይም ዘጋቢ ፊልም ኢትዮጵያ ውስጥ ለመስራት አይችልም፡፡

2/ ማንኛውም የተራኪ ወይም የዘጋቢ ፊልም ኢትዮጵያ ውስጥ ለመስራት የሚፈልግ የውጭ ዜጋ፡-

ሀ) በቅድሚያ አግባብነት ካለው የሚመለከተው አካል የድጋፍ ደብዳቤ ማምጣት ይኖርበታል፤

ለ) በደንቡና በዚህ መመሪያ መሰረት የተዘረዘሩትን መረጃዎች በማሟላት ፈቃድ ማግኘት ይኖርበታል፡፡

12. ***ስለማመልከቻ ቅፅ***

ባለሥልጣኑ የሚከተሉትን ጉዳዮች የያዘ ማመልከቻ ቅፅ ማዘጋጀት ይኖርበታል፡፡ የማመልከቻ ቅፁንም በድረ-ገፁ ተደራሽ በማድረግ ተሞልቶ እንዲቀርብ አማራጭ መንገድ ይፈጥራል፡፡

1/ የፊልም አንሽው የመጣበት አገር፣

2/ የፊልም አንሽው የሚሰራበት ተቋም፣

3/ አመልካቹ ተቋም ከሆነ ተራኪ ወይም ዘጋቢ ፊልም እንዲቀርጽ የሚያሰማራውን ባለሙያ ስም፣

4/ የስራ መደብ፣ ዜግነት፣ የፓስፖርት ቁጥር፣ ስልክ ቁጥር እና የኢሜል አድራሻ፣

13. ***የማመልከቻ አቀራረብ***

1/ በኢትዮጵያ ውስጥ ተራኪ ወይም ዘጋቢ ፊልም የሚሰራ የዉጭ አገር ዜጋ ወይም የሚዲያ ባለሙያ ወደ ሀገር ውስጥ ከመግባቱ በፊት አግባብነት ያለው አካል የሚመለከተው ኃላፊ የፈረመበት፣ የድርጅቱ ማሕተም ያረፈበት ማመልከቻ ከዚህ በታች በአንቀጽ 14 ከተጠቀሱት ዝርዝር ሰነዶች ጋር በማያያዝ ቢያንስ ከ15 ቀን በፊት በአቅራቢያው ለሚገኝ የኢፌዲሪ ኤምባሲ ወይም ቆንስላ ጄኔራል ጽሕፈት ቤት የፐብሊክ ዲፕሎማሲ ሥራ ክፍል፣ በአካል ቀርቦ ወይም በኢ-ሜል ወይም በፋክስ ወይም በሌላ አመቺ ዘዴ ማቅረብ ወይም መላክ አለበት፡፡

2/ ኢትዮጵያ ውስጥ የሚገኝ ማንኛውም ድርጅት ከውጭ ሀገር የፊልም ባለሙያ በማስመጣት ተራኪ ወይም ዘጋቢ ፊልም ማሰራት ሲፈልግ ከዚህ በታች በአንቀጽ 14 የተጠቀሱትን ማስረጃዎች አያይዞ ቢያንስ ከ15 ቀን በፊት የውጭ ሀገር የሚዲያ ባለሙያው ለሚኖርበት የኢፌዲሪ ኤምባሲ ወይም ቆንስላ ጄኔራል ጽሕፈት ቤት የፐብሊክ ዲፕሎማሲ ሥራ ለሚሰራ አካል በኢ-ሜል ወይም በፋክስ ወይም በሌላ አመቺ ዘዴ መላክ ይኖርበታል፡፡

3/ የኢፌዲሪ ኤምባሲ ወይም ቆንስላ ጄኔራል ጽሕፈት ቤት የፐብሊክ ዲፕሎማሲ ሥራ ክፍል ማመልከቻው የተሟላ መሆኑን አረጋግጦ፣ የማስረጃዎቹን አግባብነት አጣርቶ፣ ስለተራኪ ወይም ዘጋቢ ፊልሙ ጠቀሜታና ፊልም ቀራጩ ከዚህ ቀደም ስላወጣቸው የሚዲያ ውጤቶች አወንታዊነትና አሉታዊነት አስመልክቶ ያለውን አስተያየትና ተያያዥ መረጃዎችን በማካተት በሸኚ ደብዳቤ በ5 ቀናት ውስጥ በኢፌዴሪ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር በኩል ለባለስልጣን መስሪያ ቤቱ ይልካል፡፡

4/ የኢ.ፌ.ዲ.ሪ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ማመልከቻው ከነአባሪ ሰነዱ እንደደረሰው የተሟላ መሆኑን በማረጋገጥ ቢበዛ በሁለት የስራ ቀናት ውስጥ ለባለስልጣኑ ይልካል፡፡

## 14. ከማመልከቻው ጋር መያያዝ የሚገባቸው ዝርዝር ሰነዶች

1/ ተራኪ ወይም ዘጋቢ ፊልሙን ለመስራት ያመለከተው የፊልም ባለሙያ ስም፣ ዜግነት እና የፓስፖርት ቁጥር የያዘ ዝርዝር እና የፓስፖርትና የሙያ መታወቂያ ኮፒ፤

2/ ኢትዮጵያ ውስጥ የሚቆይባቸውን ቀናትና የሚዘዋወርባቸውን ሥፍራዎች፣

3/ የተራኪ ወይም የዘጋቢ ፊልሙ ቀረጻ አጠቃላይ ወጪ፣

4/ ወደ ኢትዮጵያ የሚገባበት እና ከኢትዮጵያ የሚወጣበትን ቀን፣ ሰዓት እና በአየር ትራንስፖርት የሚመጣ ከሆነ የአውሮፕላን በረራ ቁጥር፣

5. ተራኪ ወይም የዘጋቢ ፊልሙን ዓላማ በዝርዝር የሚያስረዳ ጽሁፍ፣

6. አመልካቹ ለተራኪ ወይም ለዘጋቢ ፊልም ቀረጻ የሚጠቀምባቸው የሙያ መገልገያ መሣሪያዎች ዝርዝር 2 ቅጂ እና ስራውን ሲያጠናቅቅ በዝርዝሩ ላይ የተመለከቱትን የሙያ መገልገያ መሣሪያዎችን ይዞ እንደሚወጣ ግዴታ መግባቱን የሚገልጽ በጽሁፍ የተደገፈ ሰነድ፣

7. የሙያ መሳሪያዎቹ ዝርዝር፤ የመሳሪያዎቹን ስሪት ወይም ሞዴል፣ ልዩ መለያ ቁጥር /Serial No/፣ ብዛት እና እያንዳንዳቸው የተገዙበትን ዋጋ ማካተት አለበት፡፡

## 15. አመልካቹ ወደ ሀገር ውስጥ ከገባ በኋላ ለባለስልጣኑ ማቅረብ ያለበት ማስረጃዎች

1/ የዜና ወኪል ኦሪጅናል ደብዳቤውን፣ አንድ ጉርድ ፎቶ-ግራፍ (3x4 ሳ.ሜ) የራሱንና የቡድኑን ፓስፖርትና የሙያ መታወቂያ ይዞ በባለስልጣን መስሪያ ቤቱ በግንባር በመቅረብ ከዚህ መመሪያ ጋር በአባሪነት የተያያዘውንና የተዘጋጀውን ለፊልም ቀረጻ የተዘጋጀውን ቅጽ -2- መሙላት አለበት፣

2/ አመልካቹ የማመልከቻ ቅጹን ከመሙላቱና የፈቃድ ክፍያ ከመፈጸሙ በፊት የጸና ፓስፖርት፣ የጋዜጠኝነት ቪዛ ያለው እንዲሁም በሕጋዊ መንገድ ተመዝግቦ ወደ ሀገር ውስጥ የገባ መሆኑ መረጋገጥ አለበት፣

## 16. ከአየር ላይ ፊልምና ፎቶግራፍ ለማንሳት የበረራ ፈቃድ ስለማግኘት

1/ አመልካቹ በአውሮፕላን ወይም ድሮን ከአየር ላይ ፊልም ወይም ፎቶ-ግራፍ ለማንሳት ከፈለገ ከኢትዮጵያ ሲቪል አቪዬሽን ባለሥልጣን ወይም ከመረጃ መረብ ደህንነት ኤጀንሲ የበረራ ፈቃድ ማግኘት አለበት፣

2/ አመልካቹ ከአየር ላይ ፊልም ወይም ፎቶ-ግራፍ የሚያነሳ ከሆነ ማመልከቻው የሚዲያ ባለሙያው ከመምጣቱ ቢያንስ ከ10 ቀናት በፊት ለባለስልጣኑ መድረስ አለበት፣

3/ አመልካቹ የበረራ ፈቃድ ማመልከቻውን ለባለስልጣኑ ማቅረብ አለበት፡፡

## 17. ከአየር ላይ ፊልምና ፎቶግራፍ ለማንሳት ለበረራ ፈቃድ የሚቀርብ ማመልከቻ የሚይዛቸው ዝርዝር ሰነዶች

ከአየር ላይ ፊልምና ፎቶግራፍ ለማንሳት ለበረራ ፈቃድ የሚቀርብ ማመልከቻ የሚከተሉትን ዝርዝር ሰነዶች መያዝ ይኖርበታል፡፡

1/ አውሮፕላኑን ወይም ድሮን በባለቤትነት የሚያስተዳድረው ድርጅት እና አብራሪ ሙሉ ስምና አድራሻ፣

2/ የአውሮፕላኑን ወይም ድሮን ዓይነት እና የምዝገባ ምልክት፣

3/ ወደ ኢትዮጵያ የሚገባበት ልዩ ቦታ እና የሚዘዋወርባቸውን ሥፍራዎች፣

4/ ኢትዮጵያ ውስጥ ገብቶ የሚያርፍበትንና ከአገር የሚወጣበትን ቀንና ሰዓት፣

5/ ከኢትዮጵያ የሚወጣበትን የበረራ አቅጣጫና መዳረሻ አገር በግልፅ ማመላከት ይኖርበታል።

## 18. ለፊልም ቀረጻ የቪዛ ጥያቄን ስለማስተናገድ

ለተራኪና ዘጋቢ ፊልም ስራ ወደ ኢትዮጵያ የሚመጣ የውጭ ዜጋ በሚከተሉት አሰራር መሰረት አግባብነት ያለዉ ቪዛ ሊኖረው ይገባል፣

1/ ባለስልጣኑ በዚህ መመሪያ አንቀድ 14፣15 እና 16 መሰረት የቀረበለትን ማመልከቻ ከገመገመ በኋላ ጥያቄው የተሟላ ሆኖ ሲያገኘው አመልካቹ አግባብነት ያለዉ ቪዛ እንዲሰጠው ከሶስት የስራ ቀናት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ ከኢሚግሬሽን ዜግነት እና ወሳኝ ኩነት ምዝገባ ኤጀንሲ በደብዳቤ ያሳውቃል፣

2/ ባለስልጣኑ የኢፌዲሪ ኤምባሲ ወይም ቆንስላ ጄኔራል ጽሕፈት ቤት ከሌለባቸው ሀገራት የሚመጡ የውጭ ሀገር ዜጎች ቦሌ አለም አቀፍ አውሮፕላን ጣቢያ ሲደርሱ የመዳረሻ አግባብነት ያለው ቪዛ እንዲሰጣቸው ከኢሚግሬሽን ዜግነት እና ወሳኝ ኩነት ምዝገባ ኤጀንሲ በደብዳቤ ያሳውቃል፣

3/ ኢሚግሬሽን እና ዜግነት ጉዳዮች ዋና መምሪያ የጋዜጠኝነት ቪዛ ወይም አግባብነት ያለው ቪዛ የተጠየቀላቸው የውጭ ሀገር ዜጎች ከባለስልጣኑ ደብዳቤ ሲደርሰው ቪዛ እንዲያገኙ ጥያቄውን ላቀረበው በውጭ ሀገር የኢፌዲሪ ኤምባሲ ወይም ቆንስላ ጄኔራል ጽሕፈት ቤት ይልካል፤ መላኩንም ለሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ያሳውቃል፣

4/ ባለስልጣኑ የቪዛ ጥያቄው ምላሽ ማግኘቱን ይከታተላል፣ የደረሰበትን ለሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ያሳውቃል፣

5/ ባለፈቃዱ ኢትዮጵያ ውስጥ ለመቆየት ቪዛው እንዲራዘምለት ጥያቄ ሲያቀርብና ይህም በባለስልጣኑ ተቀባይነት ሲያገኝ ከኢሚግሬሽን ዜግነት እና ወሳኝ ኩነት ምዝገባ ኤጀንሲ ቪዛው እንዲራዘምለት በደብዳቤ ይጠይቃል፣

6/ ባለስልጣኑ የጋዜጠኝነት ቪዛ/አግባብነት ያለው ቪዛ ወይም ኢትዮጵያ ውስጥ ለመቆየት የቪዛ ይራዘምልኝ ጥያቄውን ያልተቀበለው እንደሆነ ያልተቀበለበትን ምክንያትና ውሳኔውን በአንድ የሥራ ቀን ውስጥ ለአመልካቹ ማሳወቅ ይኖርበታል፣

7/ ባለስልጣኑን ምንም አይነት ፈቃድ ሳይጠይቅ ከጋዜጠኝነት ቪዛ/አግባብነት ካለው ቪዛ ውጭ በሆነ ቪዛ ሀገር ውስጥ የገባ እና ከባለስልጣኑ የተራኪ ወይም የዘጋቢ ፊልም ስራ ፈቃድ የሚጠይቅ የውጭ ሀገር ዜጋ ፈቃዱ ሳይሰጠው ከኢሚግሬሽን ዜግነት እና ወሳኝ ኩነት ምዝገባ ኤጀንሲ በሚሰጠዉ አቅጣጫ መሰረት አስተዳደራዊ ውሳኔ እንዲሰጠው ይደረጋል፣

8/ ባለስልጣኑ የኬንያና የጂቡቲ ዜግነት ያላቸው የውጭ ሀገር ዜጎች በሀገር ውስጥ የተራኪ ወይም የዘጋቢ ፊልም ስራ ለመስራት ወደ ሀገራችን መምጣት ሲፈልጉ ኢትዮጵያ ከሁለቱ ሀገራት ጋር ባላት ስምምነት መሰረት ቪዛ አይጠየቁም፡፡

## ***<u>ክፍል አራት</u>***
## ***<u>ስለምዝገባ፣ ፈቃድ አሰጣጥ እና ስለክፍያ ሁኔታ</u>***

### 19. ***<u>የምዝገባ የምስክር ወረቀት ወይም ፈቃድ ስለመስጠት</u>***

1/ ባለስልጣኑ ፈቃድ ከመስጠቱ በፊት ቀደም ሲል የዉጭ መገናኛ ብዙኃን የዜና ወኪሉ ወይም የፊልም ቀረጻ የሚሳተፈው የውጭ ዜጋ ለተመሳሳይ ሥራ ወደ ኢትዮጵያ መጥቶ የነበረ ከሆነ በጊዜው ከሥራው ጋር በተያያዘ ምንም ዓይነት የሕግ መተላለፍ ሪከርድ የሌለበት መሆኑ መረጋገጥ አለበት፣

2/ ባለስልጣኑ የዉጭ መገናኛ ብዙኃን ዜና ወኪሉ ወይም የፊልም ቀራጩ የውጭ ዜጋ የጋዜጠኝነት ወይም አግባብነት ያለዉ ቪዛ ማግኘቱን ሲያረጋግጥ የዜና ወኪሉ ወይም የተራኪ ወይም የዘጋቢ ፊልም ባለሙያው የምዝገባ ወይም የፈቃድ ክፍያ በማስከፈል፣ ጥያቄው በቀረበለት በአንድ ቀን ጊዜ ውስጥ የምዝገባ የምስክር ወረቀት ወይም ፈቃድ ይሰጣል፣

3/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 መሰረት በተሰጠ የምዝገባ የምስክር ወረቀት ወይም ፈቃድ ላይ ከተገለጹት ቦታዎች መካከል ዘገባ፣ ተራኪ ወይም ዘጋቢ ፊልም ለመሥራት ተጠይቀዉ ከሀገር ደህንነት አንጻር የተከለከሉ ቦታዎች

ካሉ ሥልጣን ያለው የመንግስት አካል የቀረጻ ፈቃድ እንዳይሰጥ የመከልከል መብቱ የተጠበቀ ነው፡፡

## 20. ስለክፍያ

1/ አመልካቹ የዜና ወኪል ምዝገባ ወይም ፈቃድ ያመለከተ ከሆነ በባለስልጣኑ የክፍያ መመሪያ ላይ በተወሰነው የክፍያ ተመን መሰረት የምዝገባ ወይም የፈቃድ ክፍያ ለባለስልጣኑ ይከፍላል፡፡

2/ አመልካቹ ፊልም ለመስራት የሚመጣ ከሆነ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 66/1992 አንቀጽ 12 ላይ በተገለጸው የአከፋፈል ስርዓት ወይም ወደፊት ተሻሽሎ በሚወጣ የክፍያ ሕግ መሰረት የፈቃድ ክፍያ ተመን መሰረት ኢትዮጵያ ውስጥ ተራኪ እና ዘጋቢ ፊልም ለመስራት የሚፈልግ የውጭ ሀገር ዜጋና የፊልም ባለሙያ የፈቃድ ክፍያ ለባለስልጣኑ ይከፍላል፡፡

3/ የፊልም ማንሳት ሥራ የሚካሄደው ፊልም ለማንሳት ክፍያ በሚያስከፍል ቦታ የሆነ እንደሆነ ለባለሥልጣኑ የሚከፈለውን ክፍያ አያስቀረውም፡፡

## 21. ከክፍያ ነፃ ስለሚስተናገዱ የውጭ መገናኛ ብዙኃን እና ሌሎች የውጭ አገር ዜጋ የሆኑ ዜና ወኪሎች

ከዚህ በታች በተመለከቱ ጉዳዮች ዜና ለመዘገብ ወደ ኢትዮጵያ የሚመጡ የሚዲያ ባለሙያዎች ከክፍያ ነጻ ይስተናገዳሉ፣

1/ ከዉጭ አገር ከፍተኛ የመንግስት አመራሮችና የልዑካን ቡድን ጋር አብረው የሚመጡ ጋዜጠኞች፣

2/ የአፍሪካ ሕብረት፣ የኢጋድ፣ የተባበሩት መንግሥታት የአፍሪካ ኢኮኖሚ ኮሚሽን እና የመሳሰሉ ጉባዔዎችን ለመካፈል የሚመጡ ልኡካን፣ ጋዜጠኛ

3/ ሀገራዊ፣ ከባቢያዊ፣ አህጉራዊና የሌሎች ዓለም አቀፍ ጉባዔዎችን እና ሁነቶችን ለመዘገብ የሚመጡ ጋዜጠኞች፣

4/ በመንግስት ግብዣ ለገፅታ ግንባታ፣ ለፕሮሞሽን፣ ለኢንቨስትመንት፣ ቃለ-መጠይቅ ለመስራት የሚመጡ የሚዲያ ባለሙያዎች፣

## 22. የአመልካቹ ግዴታዎች

የዜና ወኪልና የፊልም ቀረጻ አመልካቹ የሚከተሉትን ግዴታዎች ማክበር ይኖርበታል፡-

1/ በምዝገባ የምስክር ወረቀቱና በፈቃድ ላይ የተመለከቱ ግዴታዎችን ማክበር ይኖርበታል፤

2/ የሀገሪቱን ሕግ፣ የሕዝቦቿን ባህልና እሴቶች ማክበር ይኖርበታል፤

3/ የሃገርን ደህንነት፣ የሕዝቦችን አንድነት የሚሸረሽር፣ የጥላቻ ንግግርና ሀሰተኛ መረጃን የሚያሰራጭ ዘገባ ማሠራጨት የተከለከለ ነው፤

4/ የጋዜጠኝነት ሙያዊ ሥነ-ምግባር የተላበሰና በትክክለኛ መረጃ ላይ ተመስርቶ መንቀሳቀስ ይኖርበታል፣

5/ በማመልከቻ ጠይቆ ከተፈቀደለት ቦታ ውጪ ተገኝቶ መስራት አይፈቀድም፣

6/ ከባለስልጣኑ የተሰጠውን ምዝገባ የምስክር ወረቀት ወይም ፈቃድ ለሌላ ሶስተኛ ወገን አሳልፎ መስጠት የተከለከለ ነዉ፣

7/ ቀደም ሲል ፈቃድ ተሰጥቶት የሰራ ከሆነ የዘጋቢ ወይም የተራኪ ፊልሙን ሁለት ቅጂ ለባለስልጣኑ መላኩ መረጋገጥ ይኖርበታል።

8/ ሌሎች በአዋጁና በሀገሪቱ ህጎች የተደነገጉ ድንጋጌዎችን ማክበር ይኖርበታል፡፡

## 23. ፈቃድ ስለመሰረዝ

በዚህ መመሪያ አንቀጽ 22 በተመለከተው መሰረት የምዝገባ ምስክር ወረቀት ወይም ፈቃድ የተሰጠው ሰው የገባውን ግዴታ ያላከበረ እንደሆነ እንዲሁም አዋጁንና ሌሎች የሀገሪቱን ሕጎች ከተላለፈ የምዝገባ ምስክር ወረቀቱ ወይም ፈቃዱ በአዋጁ መሠረት ይሰረዛል፡፡

## ክፍል አምስት
## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

## 24. ከቀረጥ ነፃ መብት

1/ አመልካቹ ለዘገባ እንዲሁም ለተራኪ ወይም ዘጋቢ ፊልም ቀረጻ የሚያስገባቸው የሙያ መገልገያ መሣሪያዎችን ሥራው ሲጠናቀቅ ከሀገር መልሶ እንደሚያስወጣ ባቀረበው ማመልከቻ ላይ ግዴታ መግባቱ ሲረጋገጥ እነዚህ መሣሪያዎች የጉምሩክ ቀረጥ ሳይከፈልባቸው እንዲገቡ ይደረጋል፤

2/ አመልካቹ ከመምጣቱ በፊት ለጉምሩክ የሚጻፍለትን ደብዳቤ ለሚወክለው ሰው እንዲሰጥለት ከፈለገ እና ሥራው ሲጠናቀቅ የሙያ መገልገያ መሣሪያዎቹን እንደሚመልስ በፅሁፍ ቃል ከገባ ተወካዩ የፈቃድ ክፍያውን ከፍሎ ደብዳቤው እንዲሰጠው ይደረጋል፤

3/ ከባለስልጣኑ በተጻፈው ከቀረጥ ነጻ ክሊራንስ ደብዳቤ ላይ የሙያ መገልገያ መሣሪያዎች ቀደም ሲል በተመለከተው ከሀገር መውጫ ቀን መሰረት ንብረቱ በሚወጣበት ቦታ የሚገኙ የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን የጉምሩክ መቆጣጠሪያ ጣቢያዎች መገልገያ መሳሪያዎቹ በትክክል መውጣታቸውን የመከታተል ግዴታ ይኖርበታል፣

4/ ከባለስልጣኑ በተጻፈው ደብዳቤ ላይ በተገለጸው መሰረት ለዘገባ ወይም ለዚጋቢ ፊልም ቀረጻ ስራ ወደ ሀገር ውስጥ የገቡ የሙያ መገልገያ መሳሪያዎች በተጠቀሰው ቀን ሳይወጡ መቅረታቸው ሲታወቅ ይህንኑ ያረጋገጠው የጉምሩክ መቆጣጠሪያ ጣቢያ እጅግ ቢዘገይ በ15 ቀናት ውስጥ ለባለስልጣኑ ማሳወቅ ይኖርበታል፣

5/ ከቀረጥ ነጻ ወደ ሀገር ውስጥ የገቡ የሙያ መገልገያ መሳሪያዎች ከባለስልጣኑ እውቅና ውጭ ሀገር ውስጥ መቆየታቸው ከተረጋገጠ ፈቃዱ የተሰጠው የሚዲያ ተቋም ወይም ወኪሉ የጉምሩክን ህግ በመተላለፍ ወንጀል እንዲጠየቅ ይደረጋል፣

6/ ከቀረጥ ነጻ ወደ ሀገር ውስጥ የሚገቡ የሙያ መገልገያ መሳሪያዎችን ዓይነት በማጣራት ፈቃድ የመስጠት ሥራ የመረጃ መረብ ደህንነት ኤጀንሲ ቁጥጥር ከሚያደርግባቸውና ባለስልጣኑ ወደ ሀገር ውስጥ እንዳይገቡ በሕግ ከከለከላቸው በስተቀር ክልከላ አይኖርም፡፡

## 25. *ቅጂዎችን በነጻ ስለመስጠት*

የዜና ወኪሉ ወይም ፊልም ቀራጩ ሥራውን አጠናቆ በመገናኛ ብዙኃን ካሰራጨ ከአንድ ወር ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ የሚዲያ ውጤት 2 ቅጂዎችን ከክፍያ ነጻ በኢ-ሜል ወይም በፖስታ ወይም በሌላ አመቺ በሆነ ዘዴ ለባለስልጣኑ መላክ ይኖርበታል፡፡

## 26. *ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በቅንጅት ሥለመስራት*

ከባለስልጣኑ ፈቃድ አግኝተው ለሥራ የተሰማሩ ማናቸውም የውጭ አገር ዜጎች ወይም የሚዲያ ባለሙያዎች የገቧቸውን ግዴታዎች አክብረው እየሰሩ መሆናቸውን በተሻለ ሁኔታ ለማረጋገጥ ጉዳዩ ከሚመለከታቸው የፌዴራልና የክልል መንግሥት ተቋማት ጋር ተገቢውን መረጃ በመስጠት፣ ክትትልና ቁጥጥር ለማድረግ በቅንጅትና በትብብር ይሰራል፡፡

## 27. *መመሪያውን ስለማሻሻል*

የባለሥልጣኑ ቦርድ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ይህን መመሪያ ሊያሻሽል ይችላል::

## 28. *የተሻረ መመሪያ*

ይህን መመሪያ የሚቃረን ማንኛውም መመሪያ ትእዛዝ ወይም የተለመደ አሰራር ተፈጻሚነት አይኖረውም፡፡

29. <u>መመሪያው የሚጸናበት ጊዜ</u>

ይህ መመሪያ በባለሥልጣኑ የሥራ አመራር ቦርድ ከጸደቀበት ከግንቦት 9 ቀን 2014 ዓ.ም. ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

*የኢትዮጵያ የመገናኛ ብዙሃን ባለሥልጣን ሥራ አመራር ቦርድ*